# ራማ ሉል
**መስፍን አረጋ**

ተወርዋሪ ኮኮብ እሳት የሚተፋ
በራሱ ነበልባል ተቃጥሎ የጠፋ
በጠቆረዉ ሰማይ ነበረ በይፋ።
 ቀያኒ ዮሐንስ አድማሱ (ተወርዋሪ ኮኮብ) (በመስፍን በትንሹ የተለወጠ)

የሰዉ ልጅ እንዲያነበዉ ማታ፣ ማታ ሲጨልም
ሰማይን አርጎ ብራና፣ ኮኮብን አርጎ ቀለም
ብራናዉን በሉል መልክ፣ ወጥሮ ዙርያዉን ባለም
ቀለሙን ብራናዉ ላይ አርከፍክፎ በቀሠም
ፈጣሪ ጽፏል መጽሐፍ፣ ሽፋኑ የሆነ ጉም
በወቅቶች ተከፋፍሎ፣ የጊዜን ሂደት የሚጠቁም።
የመጽሐፉን ይዘት፣ የክፍፍሉን ትርጉም
ለቅዱስ ሄኖክ ገልጾለት በራዕይና በሕልም
በቅዱሱ በግእዝ ቋንቋ፣ በልሳነ አርያም
አንድ ባንድ ተንትኖታል፣ እየጠቀሰ በስም።
 መስፍን አረጋ (የካቲት 1፣ 2004)

## መንደርደርያ

ይህ ጦማር (article) **በራማ ሉል** (celestial sphere) ላይ የሚያተኩር ጦማር ሲሆን ጽፌ በጨረስኩትና አቅም ሲፈቅድልኝ በማሳትመዉ «**ጠፈርሲን**» (Astronomy) በተሰኘዉ መጽሐፍ ዉስጥ ከሚገኙት ምዕራፎች ዉስጥ የተወሰኑ ክፍሎችን በማዉጣጣት የተጻፈ ጦማር ነዉ።

ጦማር ማለት ጥናታዊ ጽሑፍ እንደ ማለት ሲሆን ቃሉ የተገኘዉም ጦማር (መጽሐፍ፣ ደብዳቤ፣ ክታብ) ከሚለዉ የግእዝ ቃል ነዉ። ጦማር ከሚለዉ ቃል በመነሳት ደግሞ ጦማረኛ (one who writes articles)፣ ጦማራዊ የሚሉትን ቃሎች እናገኛለን። ግሱም ሲረባ ጦመረ፣ ጡምር፣ ጦማሪ፣ ጡመራ እያለ ሲሄድ የእንግሊዘኛ አቻ ግን የለዉም። በነገራችን ላይ ጦማር የሚለዉ ቃል እየተለመደና በሰፊዉ ጥቅም ላይ እየዋለ ነዉ። ሌሎቹም ቃሎች ጊዜያቸዉን ጠብቀዉ የጦማርን ፈለግ እንደሚከተሉ ቅንጣት ጥርጥር የለኝም።

ራማ ማለት በግእዝ ሰማይ ማለት ነዉ «**ምህላነ ሰማእ እም ራማ**» (ልመናችንን ከሰማይ ስማ) እንዲል ክቡር መጽሐፍ። አርያም ደግሞ የራማ ብዥ - ማለትም ራማወች - ማለት ነዉ። እንግዲህ ራማ ወይም ራማዊ የሚለዉ ቃል celestial እና heavenly የሚሉትን የእንግሊዘኛ ቃሎች ይተካልናል ማለት ነዉ። ለምሳሌ ያህል ራማ ሉል (celestial sphere)፣ ራማዊ አካሎች (heavenly bodies) ይሆናሉ።

ጠፈር የሚለዉ የግእዝ ቃል astro- የሚለዉን የእንግሊዘኛ ፊልጡፍ (prefix) ይተካልናል። ስለዚህም ጠፈርሲን (astronomy)፣ ጠፈርሲናዊ (astronomical)፣ ጠፈርሲነኛ (astronomer) ይሆናሉ ማለት ነዉ። ጠፈርሲን ማለት እንግዲህ የራማዊ አካሎች ጥናት ማለት ሲሆን፣ ጠፈርሲነኛ ማለት ደግሞ የጠፈርሲን ባለሙያ ማለት ነዉ።

ቀያኒ (poet) ማለት የቅኔ ሰዉ (ባለቅኔ) ማለት ሲሆን፣ ከያኒ (artist) ማለት ደግሞ የኪነት ሰዉ ማለት ነዉ። «አርቲስት» የሚለዉ የባዕድ ቃል «ሳይቸግር ጤፍ ብድር» የሚያሰኝ ቋንቋን የሚበክል ፀያፍ - እደግመዋለሁ ፀያፍ - ቃል ነዉና ሊወገድ፣ ተሸቀንጥሮ ሊጣል፣ ይገባዋል። «አርቲስት ጥላሁን ገሰሰ፣ አርቲስት ካሳ ተሰማ፣ አርቲስት ብዙነሽ በቀለ፣ አርቲስት አስናቀች ወርቁ ወዘተ.» ማለት ደግሞ ላገራቸዉ ሕዝብ፣ ባገራቸዉ ቋንቋ ታላላቅ አስተዋጽኦወችን ያበረከቱትን ድንቅየ የጦቢያ ልጆች ከመዘለፍ የሚቆጠር ሰቅጣጭ አጠራር ነዉ።

በተመሳሳይ ሁኔታ - እኛ ጦቢያዉያን ስንባል ጥሎብን ራሳችንንና የራሳችንን በጣም ዝቅ ሌሎችንና የሌሎችን ደግሞ በዚያዉ አንጻር በጣም ከፍ ማድረግ ስለሚቀናን ነዉ እንጅ - ካለም ታላላቅ ቀያኒያን (poets) ቢበልጡ እንጅ በምንም ረገድ የማያንሱትን ታላቁን ጦቢያዊ ቀያኒ (poet) **ክቡር ከበደ**

**ሚካኤልን** «ዶክተር ከበደ ሚካኤል» እያሉ መጥራት እሳቸዉን ማንኳሰስ ነዉ። እሳቸዉ መባል ያለባቸዉ «**አለቃ ከበደ ሚካኤል**» ነዉ፣ መደባቸዉ ከታላላቆቹ ጦቢያዉያን ሊቃዉንት ከነ **አለቃ ኪዳነወልድ ክፍሌ** እና **አለቃ ደስታ ተክለወልድ** ጋር ነዉና። ያለቅነት ማዕረግ ምን ያህል ከፍተኛ እንደሆነ ለመገንዘብ ደግሞ የእዉቆቹን ጦቢያዊ ነብታሚወች (professors) **የሁሉንም ሁሉንም ሥራወች** በጥቅሉ ወስዶ «**ዐዲስ ያማረኛ መዝገበ ቃላት**» ከተሰኘዉ ካለቃ ደስታ ተክለወልድ **ካንዱ** ነጠላ ሥራ ጋር ብቻ ማነጻጸር ይበቃል።

እግረመንገዳችንን ጎተጎተ (ነቀነቀ፣ አጣደፈ፣ አስቸኮለ፣ እረፍት ነሣ፣ ወተወተ፣ ነዘነዘ) ከሚለዉ ያማረኛ ቃል ጎትጓች (activist) እና ጉትጎታ (activism) የሚሉትን ቃሎች እናገኛለን። ጎትጓች ማለት ለቆመለት ዓላማ ሽንጡን ገትሮ የሚከራከር፣ በጽኑ የሚታገል፣ ሳይታክት የሚወተዉት እንደ ማለት ሲሆን ግሱም ሲረባ ጎተጎተ (be activist)፣ ጉትጉት፣ ጎትጓች፣ ጉትጎታ እያለ ይሄዳል። ለምሳሌ ያህል **ጎትጓች ታማኝ** በየነ ማለት እንችላለን። በዚህ አጋጣሚ ደግሞ ታማኝን ትልቅ ሥራ እየሠራህ ነዉና በርታ፣ አብሔር (God) - የጦቢያ አምላክ - የበለጠና የበለጠ ያበርታህ ልለዉ እወዳለሁ።

ፈላሻ እና ዘር የሚሉትን ቃሎች በማጣመር ደግሞ ፈላሽር (diaspora) እና ፈላሽራዊ (of diaspora, diasporic) የሚሉትን ቃሎች እናገኛለን። ፈላሽር ማለት በባዕድ አገር ኗሪ ማለት ሲሆን፣ ግሱም ሲረባ ፈለሸረ (become diaspora)፣ ፍልሽር፣ ፈልሻሪ፣ ፍልሸራ እያለ ይሄዳል። ፈለሸረ ማለት እንግዲህ ፈላሽር ሆነ ማለት ሲሆን የእንግሊዘኛ አቻ ግን የለዉም።

## *ጠፈርሲን*

የጠፈርሲን ጥናት የተጀመረዉ ጥንት ኩሽ ይባል በነበረዉና በቀድሞ ጊዜ የጥቁር ሕዝብ አገር የነበረዉን ምድር ሁሉ የሚያጠቃልል በነበረዉ ምድር ዉስጥ ነበር። ይህም የጥቁሮች ምድር ታላቁን በረሐ ሰሐራንና ዛሬ ግብጽ የሚባለዉን የጥንቱን ከመትን ጨምሮ መላዉ አፍሪቃን ወዲያ ማዶም - አሁን ትናትና ወደ እስያ ክፍል የተደመሩትን - አረብ ከጥቁር ነጥቆ የሰፈረባቸዉን ሳዉዲያ አረቢያ፣ የመን፣ ኦማንን እና ከነሱ በላይ የሚገኙትን ትናንሽ አገሮችና ሐከሎች (oasis) የሚያጠቃልል ታላቅ ምድር ነበር።

የጠፈርሲን (astronomy) አባቶች ናቸዉ እየተባሉ በነጭ የቱልቀዳ (propaganda) ጃካ ሂርሳኮች (mass media) - ማለትም መገናኛ ብዙሃን - ያለመታከት ቀን ከሌት ቱልቱላ የሚነፋላቸዉ ግሪኮች ዛሬ ግሪክ ከሚባለዉ አገር ላይ ከመስፈራቸዉ አስቀድሞ - እጅግ በጣም አስቀድሞ - ከብዙ ሺ ዓመታት በፊት ታላቁ የጦቢያ ሊቅ ሄኖክ፣ የራማ አካላትን (celestial bodies) ራማዊ ሑሰት (celestial motion) እና ባሕሪ «**መጽሐፈ ሄኖክ**» በተባለዉ መጽሐፉ ዉስጥ እጅግ በሚጥም፣ ከማር በሚጣፍጥ ዘይቤ በግእዝ ልሳን አንጠርጥሮና አብጠርጥሮ ጽፎታል። ለምሳሌ ያህል

- ጨረቃ የራሷ ብርሃን እንደሌላትና የምታበራዉም የፀሐይን ብርሃን በመፀብረቅ (reflect) እንደሆነ ለመጀመርያ የተገነዘበዉ ሄኖክ ነዉ[1]።
- የፀሐይና የጨረቃ ዘዌያዊ ገማዘንግ (angular diameter) በቅርበዛ (approximately) እኩል እንደሆነና ሆንዳላዊ የፀሐይ ግርዶሽ (total solar eclipse) የሚከሰተዉም በዚሁ ምክኒያት እንደሆነ የገለጸዉ ሄኖክ ነዉ[2]።
- ወደ አድማስ በጭራሽ ሳይጠልቁ ምድርን የሚሑሩ ኮኮቦች (በዘመናዊዉ አጠራር ሠቅዋልታዊ (circumpolar) የሚባሉ ኮኮቦች) እንዳሉ የጻፈዉ ሄኖክ ነዉ[3]።
- የጨረቃን ሻጃወች (phases) ማለትም መልኮች እየተቀያየሩ ጨረቃ ሙሉ (full)፣ ሐኔ (crescent)፣ ሰኒም (gibbous) የምትሆነዉ የፀሐይ ብርሃን የሚያገኘዉ የጨረቃ ፊት ከምድር ስለሚዟዟር እንደሆነ ያብራራዉ ሄኖክ ነዉ[4]።
- ፈለኮች (planets) ፀሐይን እንደሚሑሩ ለመጀመርያ ጊዜ የተገነዘበዉና እነዚህ ፈለኮች ለፀሐይ የተገዙ መሆናቸዉን ለማሳየት በግዕዝ ቅኑይ (የተገዛ፣የተነዳ) ብሎ የሰየማቸዉ ሄኖክ ነዉ[5]።
- የራማዊ አካላትን በተለይም ደግሞ የፀሐይንና የጨረቃን ሑሰት (motion) ለመግለጽ ይረዳዉ ዘንድ ራማ ሉልን (celestial sphere) ማለትም ጠፈርን ለተለያዩ መስኮቶች (በዘመናዊዉ አጠራር ቀኝ እርገት (right ascension) እና ዝቅዝቀት (declination) ለሚባሉት) ለመጀመርያ ጊዜ የከፋፈለዉ ሔኖክ ነዉ።
- ዓመትን ለ 364 ዕለታት የከፋፈለዉ ሄኖክ ነዉ[6]።

- እያንዳንዱን ዕለት ለ 18 ሽንሽኖች የሸነሸነዉ (በዘመናዊዉ አጠራር ለሃያ አራት ተሸንሽኖ ሰዓት ለሚባለዉ) ሄኖክ ነዉ[7]::

ባጠቃላይ ሲታይ «**ዘመናዊ ጠፈርሲን**» (Modern Astronomy) ማለት ሌላ ምንም ማለት ሳይሆን «**መጽሐፈ ሄኖክ**»ን፣ በተለይም ደግሞ ከምዕራፍ 21 እስከ ምዕራፍ 25 ያለትን ክፍሎች አብራርቶና አስፋፍቶ እንደገና መጻፍ ማለት እንጅ ሌላ ምንም አዲስ ነገር የለዉም:: በርግጥም ብልሁ ንጉሥ «ከፀሐይ በታች አዲስ ነገር የለም»[8] ያለዉ መጽሐፈ ሄኖክን አንብቦ ወይም ስለይዘቱ ተነግሮት መሆን አለበት::

ነገርን ነገር ያነሳዋልና እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ «መጽሐፈ ሄኖክ» ተጽፎ ይገኝ የነበረዉ፣ የመጹስ (bible) መምሕራን ይልቁንም ደግሞ የመጀመርያዉን የግእዝን መዝቃል (dictionary) የመዘቀለዉን ኦግስቲን ዲልማንን (Augstin Dillman) ጨምሮ አያሌ የጀርመን ሊቃዉንት «**ወኮነ ኩሉ ምድር አሐተ ከንፈረ ወአሐደ ነገረ**»[9] ያለዉን ይዘዉና ተመርኩዘዉ «የአዳም ቋንቋ ነዉ» በማለት በሙሉ ድፍረት በተናገሩለት በግእዝ ልሳን ብቻ መሆኑ፣ ስለ ንጉሥ ሶሎሞን ትክክለኛ ማንነት ወደ የት ያመራናል?

ሌላዉ ሁሉ ቢቀር እንኳን ኩሽን የሚያህል በስልጣኔ የገፋ፣ ዲካ የሌለዉ እጅግ ሰፊ ምድር ትገዛ ነበር ትባል የነበረች፣ ሐብቷ ልክ ያልነበረዉ ንግሥት፣ በዚህ ዘመን ይቅርና በጥንት ዘመን እንኳን ከበሬ ግንባር ትቆጠር የነበረችን ምድር ይገዛ ወደነበረ አናሳ ንጉሥ ጥበብን ፍለጋ ሄደች የሚባለዉ ነገር በጭራሽ የማይመስል ነገር ነዉ:: ዉሃ አይቋጥርም:: በጽሞና ሳሰላሰለዉ ሰዉ ነገሩ የሚመስለዉ እዚህ ግባ የማይባለዉ ኢምንቱ ንጉሥ በዚህም በዚያም ብሎ ከግዙፏ ንግሥት ጋር በመጠጋት ራሱን ከፍ ለማድረግ የፈጠረዉ እንቶ ፈንቶ ተረት እንደሆነ ብቻ ነዉ:: በዚህ መሠረተ ቢስ እንቶ ፈንቶ ላይ ያገርን ታሪክ መገንባት ደግሞ ሌላ ምንም ሳይሆን በድቡሽት ላይ ቤት መሥራት ነዉ:: «ባህያ ቁርበት የተሠራ ቤት፣ ይፈራርሳል ጅብ የጮኸ ለት::»

መጽሐፍ ሄኖክን ያነበበ ማናቸዉም ሰዉ፣ ይህ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በግእዝ ቋንቋ ብቻ ተጽፎ ይገኝ የነበረ መጽሐፍ ከሌሎቹ የመጹስ (bible) መጻሕፍት ጋር እንዳይደመር አዉሮጳዉያን ለምን በጽኑ እንደሚቃወሙና እንደሚታገሉ በቀላሉ ሊገነዘብ ይችላል፣ እነሱ ለመጀመርያ ጊዜ አገኘናቸዉ ወይም ገለጽናቸዉ የሚሏቸዉን ጠፈርሲናዊ ክስተቶች (astronomical phenomena) ሁሉ አፍሪቃዉያን በ ሺ በሚቆጠሩ ዓመታት ከነሱ አስቀድመዉ ጠንቅቀዉ ያዉቋቸዉ እንደነበር ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ቋሚ ምስክር ነዉና:: በተጨማሪም ደግሞ ይህ አንባቢ ያፍሪቃን ወጣቶች በማኮላሸት አፍሪቃን ለዳግም ቅኝ ግዛት ለማዘጋጀት ታቅደዉ ተግባራቸዉ አንድ ቢሆንም እንኳን ፕሮቴስታንት፣ ሉተራን፣ ጴንጤ፣ ጅሆቫ፣ መካነየሱስ፣ ሙሉወንጌል ወዘተ. በመባል በተለያዩ ስሞች እየተጠሩ በጦቢያና በሌሎቹም የጥቁር አፍሪቃ አገሮች ላይ እንደ ሰደድ እሳት በመስፋፋት ላይ ያሉት መጤ «የክርስትና» ሐይማኖቶች «መጽሐፈ ሄኖክን» ለምን «የጣኦት መጽሐፍ» እያሉ እንደሚሳለቁበት በቀላሉ ሊረዳ ይችላል::

አፍሪቃዉያን በተለይም ደግሞ ደቀሔርፈናኞች (christians) ታላቁ አፍሪቃዊ አርበኛ ጆሞ ኬንያታ (Jomo Kenyata)፣ ***«አዉሮጳዉያን መዱስ የሚሰጡን፣ ለመጸለይ ዓይናችንን ስንጨፍን መሬታችንን ለመዉሰድ ነዉ»***[10] በማለት የሰጧቸዉን ምክራዊ ማስጠንቀቂያና ትንቢታዊ ቃል መቼም ቢሆን መርሳትና መዘንጋት የለባቸዉም:: ከጆሞ ኬንያታ ጋር እንደ መፎካከር ካልተቆጠረብኝ ደግሞ እኔም መደዴዉ መስፍን አረጋ ጊዜ በማይሽረዉ ከሳቸዉ ዘላለማዊ ምክር ላይ «**ዉሃቢወች ቁርዓን የሚሰጡን፣ ለመስገድ ስንንበረከክ፣ አንገት አንገታችንን መትረዉ አፍሪቃን የራሳቸዉ ለማድረግ ነዉ**»[11] ብየ በመጨመር አፍሪቃዊ ወገኖቸን በተለይም ደግሞ ሙሔፈናኞችን (Muslims) ማለትም ባረበኛዉ አጠራር ሙስሊሞችን ማሳሰብ እወዳለሁ::

ይህ የኔ ማሳሰቢያ የተጋነነ ወይም ከዉነት የራቀ አይደለም:: ዐረቦች የቱታንካሃመን (Tutankhamen) እና የሌሎች ታላላቅ ጥቁር ፈርኦኖች አገር የነበረችዉን ኑባን ማለትም በዘመኑ አጠራር ግብጽን እና የታላቁን የጦር አበጋዝ የአልፕስ (Alps) ተራራን ጌታ የአብራሃም ሐኒባል (Hannibal) አገር የነበረችዉን ያሁኒቷን ቱኒዚያን ጨምሮ መግሬብ (Meghreb) በመባል የሚታወቁትን የሰሜን አፍሪቃን አገሮች ሁሉ የሚያጠቃልለዉን ምድር በመዉረስ የግላቸዉ ሊያደርጉት የበቁት፣ ሐይማኖትን መሳርያ አድርገዉ በመግባት ነዋሪወቹን ጥቁሮችን ሴት፣ ሕፃን፣ አረጋዊ ሳይሉ ያለምንም ርህራሄ በሰየፍ እየመተሩና በእሳት እያቃጠሉ ሁሉንም ጨፍጭፈዉ ድምጥማጣቸዉን በማጥፋት ነበር:: አሁንም፣ በዚች ባሁኑ ሰዓት፣ በኛ ጊዜ ይህን ጭፍጨፋቸዉን በማናለብኝነት በዳርፉራዊ ወንድሞቻችን ላይ

በሰፊዉ እያካሄዱት ይገኛሉ:: ይህ አረመኔያዊ ድርጊታቸዉ ባጭሩ ካልተቀጨ፣ ሱዳንም ልክ እንደ መግሬብ አገሮች አፍሪቃዊ አሻራዋ ጠፍቶ ሙሉ በሙሉ ያረብ ምድር የምትሆንበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም:: የሱዳንን ሲጨርሱ ደግሞ ፊታቸዉን ወዴት እንደሚያዞሩና በቀጥታ ወዴት እንደሚያመሩ መናገር አያስፈልግም፣ ለማንም ግልጽ ነዉና::

ይቅርታ:: በስሜት ተገፋፍቸ ከተነሳሁበት ርዕስ በጣም የወጣሁ - ያፈነገጥኩ - መሰለኝ:: ባጭሩ ለማለት የፈለኩት ዉሃቢወችን (Wuhabists) ባጠቃላይም የአረብ ብሔርፈናኞችን (Arab nationalists) ከሁሉም በላይ የሚያሳስባቸዉ ጉዳይ ሙሔፍና ማለትም ባረበኛዉ አጠራር እስልምና ሳይሆን፣ የጅጋሽከታዊ ጥቅማቸዉ (geopolitical interest) መጠበቅ፣ የቋንቋቸዉ መስፋፋት፣ የባሕላቸዉ መንሰራፋት፣ የመሰፈርያ ለም ምድር ማግኘት ብቻ ነዉ:: ሙሔፍና ለነሱ ሌላ ምንም ሳይሆን የጥቅማቸዉ ማስከበሪያ መሳርያ ብቻና ብቻ ነዉ:: ለነሱ የቅዱስ ጦርነት - የጅሐድ (Jihad) - ትክክለኛ ዉ አላማ መቶ በመቶ መሔፈናኝ የሆኑት ዳርፋራዉያን ጥቁሮች መታለላቸዉ እንደ እግር እሳት እያንገበገባቸዉ በቅርቡ እንደተገነዘቡት ሙሔፍናን በሐይማኖትነቱ እንደ ሐይማኖት ለመከላከል የሚደረግ ጦርነት ሳይሆን፣ ያፍሪቃን ጥቁሮች ጨፍጭፈዉ ድምጥማጣቸዉን በማጥፋት መሬታቸዉን መሉ በሙሉ ተቆጣጥረዉ ያረብ መሬት፣ ያረብ ርስትና ጉልት ማድረግ ነዉ::

እርግጥ ነዉ ይህ አመለካከቴ የማይጥማቸዉ የገዛ አገሬ - የጦቢያ - የዋህ ጥቁር ሙሔፈናኞች፣ በአረብ ባሕልና በሙሔፍና መካከል ያሉትን ሰፊ ልዩነቶች ጠንቅቀዉ የማያዉቁ ጥቁር ሙሔፈናኞች፣ የራሳቸዉን ጥበብና ሽማ ጥለዉ ያረብን ዝተት የሚለብሱና የሚከናነቡ ጥቁር ሙሔፈናኞች፣ ከራሳቸዉ ቋንቋ ይልቅ አረበኛን የሚመርጡና ልጆቻቸዉን ሁሉ በራሳቸዉ ቋንቋ ሳይሆን ባረብኛ ሙሐመድ፣ ከድር፣ አቦከር ወዘተ. እያሉ የሚሰይሙ ጥቁር ሙሔፈናኞች፣ አረቦች ለጥቅማቸዉ ማስከበርያ ከመጠቀም በቀር ለሙሔፍና ዴንታ እንደሌላቸዉ ግልጽ የሆነዉ ሐቅ የማይታያቸዉ ጥቁር ሙሔፈናኞች፣ ስማቸዉን መጥቀስ የማያስፈልግ የለየላቸዉ ያረብ ዋቆቢሶች (atheists) የሌላዉን ዓለም ሙሔፈናኞች ድጋፍ በማግኘት ብሔርፈናኝ ፋሮራቸዉን (nationalist agenda) ለመገብረት (apply) ሲሉ ብቻ ቁርዓንን ሲጠቅሱ ዓይናቸዉን የማይከፍቱ፣ እንዴት ወይም ለምን ብለዉ የማይጠይቁ ጥቁር ሙሔፈናኞች፣ ከራሳቸዉ አገር ይልቅ (አብዛኞቹ ባይሆኑም እንኳን ጥቂቶቹ) ላረብ አገሮች ለመሞት ዝግጁ የሆኑና ታጥቀዉ የተነሱ ጥቁር ሙሔፈናኞች፣ ባረቦች ለሚጨፈጨፉት ለወንድሞቻቸዉ ለጥቁር ዳርፋራዉያን ከማዘንና ከመቆጨት ይልቅ፣ ለፓልስቲኖችና ለኢራቆች ዘወትር የሚያለቅሱና የሚያላዝኑ ከራሳቸዉ ከፓልስቲኖችና ከኢራቆች ይልቅ ለነሱ የበለጠ የሚጨነቁ - እንቅልፍ የሚያጡ - ጥቁር ሙሔፈናኞች - እንዳሉ የሚያከራክር አይደለም::

ይሁንና በዚህ እምነቴና አመለካከቴ ሳቢያ ያገሬ ባጠቃላይም ጥቁር ሙሔፈናኞች እኔን የተዋህዶ ሐይማኖት አፍቃሪ፣ የሙሔፍና ጠላት አድርገዉ እንደማያዩኝ ተስፋ አደርጋለሁ:: ሐይማኖቴ ጦቢያፍና (Ethiopianism) እንጅ ደቀሔርፍናም (christianity) ሙሔፍናም (Islam) አይደለም:: በየትኛ ዉም መንገድ - በምንም ዓይነት መነጽር - ቢመለከቱኝ እኔ ፀረሙሔፍና ልሆን አልችልም:: ትዉልዴም ቢሆን ሕዝቦች በሐይማኖትና በዘር ሳይለያዩ በመፋቀር በሚኖሩበት፣ ተስማምቶና ተከባብሮ በሰላም መኖርን በተግባር በማሳየት ለመላዉ ለዓለም ተምሳሌት በሆነዉ በደጋጎቹ ምድር በወሎ ዉስጥ የሆነ ወሎየ ነኝ:: እኔ ሙሔፍናን ከማክበር በስተቀር በሌላ በምንም ዓይን አልመለከተዉም:: ነገር ግን አረቦችን ለማወቅ እንዲረዳኝ ከመጠቀም በስተቀር ላረቦች ቋንቋና ባሕል ዴንታ የማይሰጠኝ፣ በራሴ ቋንቋና ባሕል የምኮራ ጥቁር አፍሪቃዊ ነኝ:: የኔ ሙከራ ሙሔፍናን ወይም ሙሔፈናኞችን ለመተቸት ወይም ለማንቋሸሽ ሳይሆን የዋሆቹ ያገሬ ሙሔፈናኞች ያረብ ብሔርፈናኞችን (Arab nationalists) ድብቅ ፋሮራ (agenda)፣ ማለትም ሙሔፍናን በመጠቀም ጅጋሽከታዊ ጥቅማቸዉን ለማስከበር ያላቸዉን መሰሪ ዓላማ ዓይናቸዉ ከፍተዉ እንዲመለከቱ፣ /ሳይበሉ/ በፊት እንዲነቁበት፣ «እኛም አዉቀናል ጉደኀድ ምሰናል» እንዲሉ ለማድረግ ብቻ ነዉ::

«መጽሐፈ ሄኖክ» በግእዝ ከተጻፈ ከብዙ ሺ ዓመታት በኋላ፣ መወለድ ይቅርና ገና ያልተፀነሱት ትናንት መጤወቹ ባዕዳን ቋንቋወች (በተለይም ደግሞ እንግሊዘኛና በመጠኑም ቢሆን ሐይማኖትን አስታኮ ዐረብኛ) የግእዝ አንጋፋ[12] ልጅ የሆነዉን፣ አስፈላጊወቹ ቃሎች የሰዋሰዉ ሕጎችን ተከትለዉ በቀላሉ /እንዲራቡ/ ሁነዉ እስከተፈጠሩለት ድረስ ማናቸዉንም ፅንሳቦች[13] (concepts) ግሩም አድርጎ መግለጽ የሚችለዉን፣ እንደ ልብ የሚተጣጠፈዉን፣ እንዳበጁት የሚበጀዉን፣ ከማር የሚጣፍጠዉን፣ ማራኪዉን ቋንቋ አማረኛን ደምስሰዉ ከምድር ገጽ ሊያጠፉት በያቅጣጫዉ እያዋከቡት፣ በገዛ ቤቱ ዉስጥ ኳዳ ለኳዳ ያራዉጡት ይዘዋል:: ሁኔታወች በዚህ መልክ ከቀጠሉ ደግሞ ጥረታቸዉ ባጭር ጊዜ

ዉስጥ ተሳክቶ፣ አማረኛችን እንዳሚያከትምለት ሳይታለም የተፈታ ነዉ። አማረኛ ሲያከትምለት ደግሞ የኛም ማንነት ካማረኛ ጋር አብሮ ያከትማል፣ ቋንቋ ማንነት ነዉና።

የወያኔም አንዱና ዋናዉ ዓላማ ይሄ ይመስለኛል፣ አማረኛን ቀስ በቀስ በመግደል የጦቢያዉያንን መተሳሰርያ ገመድ በጣጥሶ ጦቢያን ብትንትኗን ማዉጣት። ለዚህ ነዉ ያማረኛ አቻቸዉን እየጣለ ኤጀንሲ፣ ዞን፣ ሳጅን፣ ኢንስፔክተር፣ ትራንስፎርሜሽን ... ምንትሴ፣ ቅብጥርሴ እያለ - የሚጨመላለቀዉ ማለት ፀያፍ ቢሆንብኝም - የሚበሽቃቀጠዉ። ወያኔ ይሄን ቢያደርግ ገና ከጅምሩ ጀምሮ ሽንጡን ገትሮ የቆመለት አብይ ዓላማዉ ስለሆነ ሊያስገርመንም ሆነ ሊያስደንቀን አይገባም። በጣም የሚያስገርሙትና እጅግ የሚያሳዝኑት ግን አዉቀዉም ሆነ ባለማወቅ ወያኔ በቀደደላቸዉ የጥፋት ቦይ በገዛ ፍቃዳቸዉ /የሚፈሱት/ የኔ ቢጤ ተላሎች ናቸዉ።

የዛሬይቱ ጦቢያ «አማረኛ መናገርና ዲንጋ መወርወር ያስቀጣል» የሚባልባት፣ ልጆቻቸዉ ቋንቋቸዉን ባለማወቃቸዉ የሚኮሩ፣ ተዋርደዉ አዋራጅ ደንቆሮ ወላጆች እንደ አሸን የፈሉባት፣ «ኒዉዮርክ ካፌ»፣ «ዋሽንግተን ባር»፣ «ኀይሌ ሪዞርት»፣ «ሐርሞኒ ሆቴል»፣ «ሰንሻይን ኮንስትራክሽን»፣ «አክሰስ ሪል ስቴት»፣ «ፍሬንድሽፕ ሕንፃ»፣ «ሌክስ ፕላዛ»፣ «ፋንታስቲክ ሳሙና»፣ «ሴንሴሽን ኮንዶም»፣ «ደሴ ስፕሪንግ»፣ «ሃይላንድ ዉሃ» የመሳሰሉ አሳፋሪና አጸያፊ ስሞች በየቦታዉ የተገጠገጡባት፣ ሌላዉ ቀርቶ በጦቢያ ሕዝብ አንጡራ ሐብት በሚሠሩ መንገዶች ላይ የመንገድ ምልክቶች በእንግሊዘኛ ብቻ የሚጻፉባት እጅግ በጣም በሚዘገንን ሰቅጣጭ ሁኔታ ላይ ያለች ያልታደለች ምስኪን አገር መሆኗን መዘንጋት የለብንም።

ለዚህ ሁሉ መዉደቅ፣ መድቀቅና መላሸቅ አንዱና ዋናዉ ምክኒያት የተቃራኒ ሐሳቦች በነጻ መንሸራሸር ባገራችን ዉስጥ ለረዥም ዘመናት በከፍታኛ ደረጃ መታፈኑና፣ በዚህም ምክኒያት ቋንቋና ራስን የማክበር ባህል አለመዳበሩ ነዉ። እነ ዘርዓያቆብንና ወልደሂወትን የመሳሰሉት ፈላስፎቻችን ሲፈላሰፉ መናፍቅ፣ ዐላዊ[14]፣ ሐሳዊ[15]፣ እነ አለቃ ኪዳነወልድ ክፍሌንና አለቃ ደስታ ተክለወልድን የመሳሰሉት ታላላቅ ጸሐፊወቻችን ሲጽፉ፣ ብራና ፋቂ፣ መጽሐፍ ገላጭ፣ ቀለም በጥባጭ፣ ተመራማሪወቻችን ሲመራመሩ፣ ጠንቋይ፣ ጠጠር ጣይ፣ ኮከብ ቆጣሪ፣ ጠቢቦቻችን ሲጠበቡ ሸክላ ቧጣጭ፣ ብረት አዝባጭ፣ ሥር ማሽ፣ ቅጠል በጣሽ ..... እረ ስንቱን ብየ ልዝለቀዉ ...... እየተባሉ ይዘለፋሉ፣ ይሰደባሉ፣ አልፎ ተርፎም ይወገዛሉ፣ ይጋዛሉ፣ ይሰደዳሉ፣ ይታሰራሉ፣ ይገደላሉ። ሐሳቡን በነጻ ከመግለጽ የታፈነ ሕዝብ ደግሞ ሲጨንቀዉ ሐሜት፣ ሽሙጥ፣ አሽሙር፣ ሽርደዳ፣ ምፀትና[16] ለበጣ[17] በመሳሰሉት ዘዴወች ስሜቱን ይተነፍሳል። በዚህ ምክኒያት ነዉ እነዚህ አኩይ ባሕርያት እኔን መስፍንን ጨምሮ ባብዛኞቻችን ጦቢያዉያን ላይ መረን ተለቀዉ፣ ሥር ሰደዉ፣ ሰፍተዉና ተንሰራፍተዉ የሚገኙት።

ዋሻ ዉስጥ የሚተኛ - ባራት እግሩ ሂያጅ
አሕዛብ[18] የነበረዉ - አረመኔዉ ፈረንጅ፣
ዛሬ ተብሎ ጠቢብ - በስልጣኔ ፏዳጅ[19]
በትረ ሥልጣን ቢጨብጥ - የበላይነት ቢቀዳጅ፣
ቢገዛን እየረገጠ - እየገረፈ ባኮርባጅ
ቢሸጠን እየቀየደ[20] - እያሰረ በፍንጅ[21]
ቢመለከተን እየናቀ - እያሳነሰ ከዉሻ ልጅ
ባዲስ ግኝት አይደለም - በኛዉ ጥበብ እንጅ፣
እያልነዉ ቁጢት በጣሽ - ቀጥቃጭና ባለጅ
እኛዉ እያረከስነዉ - በልፈፋ[22]፣ ባዋጅ
ንቀን የጣልነዉን - ብለነዉ አዋራጅ።
ነጭ ብልጥ ሁኖ - ለራሱ የሚበጅ
አገሩን ሊያለማ - ሐብቱን ሊያደረጅ
ሞፈሩን ቆረጠ - ከሞኝ ጥቁር ደጅ።

ለማንኛዉም ወደ ተነሳሁት ርዕስ ማለትም ወደ ራማ ሉል ልመለስ። ስለ ራማ ሉል ከመወያየታችን በፊት ግን ከሚከተሉት ቃሎች ጋር መተዋወቅ ያስፈልገናል።

## *የቃላት መግቢያ*

ሩቅ ከሚለዉ ያማረኛ ቃል ሩ (tele- ) የሚለዉን ፊልጡፍ (prefix) እናገኛለን:: አይፊያ (አይን) ከሚለዉ የወላይትኛ ቃል ደግሞ ፓይፋ (-scope) የሚለዉን ኃልጡፍ እናገኛለን:: እንዚህን በማጣመር ደግሞ ሩፓይፋ (telescope)፣ ሩፓይፋዊ (telescopic) የሚሉትን ቃሎች እናገኛለን:: ሩፓይፋ ማለት «የሩቅ መመልከቻ መነጽር» ማለት ነዉ::

ወልፌኬኛ (ያዉ) ከሚለዉ የኦሮምኛ ቃል ወልፌክ (constant) የሚለዉን ቃል እናገኛለን:: ግሱም ሲረባ ወለፈከ (become constant)፣ ዉልፍክ፣ ወልፋኪ፣ ዉልፈካ እያለ ይሄዳል:: እግረመንገዳችንን ጌደረማ (ተለዋወጠ) ከሚለዉ የኦሮምኛ ቃል ገድራሚ (variable) የሚለዉን ቃል እናገኛለን:: ግሱም ሲረባ ገደረመ (vary)፣ ግድርም (varied)፣ ገድራሚ (varying, variable)፣ ግድረማ (variation) እያለ ይሄዳል::

አፈነፈነ እና አገኘ የሚለዉትን ቃሎች በማጣመር ፈነገነ (detect) የሚለዉን ግስ እናገኛለን:: ግሱም ሲረባ ፈነገነ፣ ፍንግን (detected)፣ ፈንጋኝ (detector)፣ ፍንገና (detector) እያለ ይሄዳል:: ስለዚህም ፈንጋኝ፣ ፍንገናዊ (detective) ይሆናሉ:: ፈነገነ ማለት አፈንፍኖ አገኘ እንደ ማለት ነዉ:: ለምሳሌ ይህል ብራኑስ ፈንጋኝ (photon detector)፣ ተልኑስ ፍንገና (electron detection) ይሆናሉ::

በርባዳ (ማግኘት) ከሚለዉ የኦሮምኛ ቃል በረበገ (discover) የሚለዉን ቃል እናገኛለን:: በረበገ ማለት አገኘ እንደ ማለት ሲሆን ግሱም ሲረባ በረበገ፣ ብርብግ (discovered)፣ በርባጊ (discoverer)፣ ብርበጋ (discovery) እያለ ይሄዳል:: ከዚህም በርበግ (discovery)፣ ተበርባጊ (discoverable)፣ ተበርባጊነት (discoverability) የሚሉትን ቃሎች እናገኛለን:: በርበግ ማለት የተበረበገ ማለትም የተገኘ ነገር ማለት ነዉ:: በሌላ አባባል በርበግ ማለት ግኝት ማለት ነዉ::

ዱካ እና ፋና የሚሉትን ቃሎች በማጣመር ነዉ ዱክፋን (pattern) የሚለዉን ቃል እናገኛለን:: ግሱም ሲረባ ደከፈነ (to form pattern)፣ ድክፍን (patterned)፣ ደክፋኝ፣ ድክፈና (pattern formation) እያለ ይሄዳል:: ዱክፋን ማለት ቅርጽ፣ ምስል እንደ ማለት ነዉ::

ዳበዳ (መቆም) ከሚለዉ የኦሮምኛ ቃል ደበደ (fix) የሚለዉን ግስ እናገኛለን:: ግሱም ሲረባ ደበደ፣ ድብድ (fixed)፣ ደባጅ፣ ድበዳ (fixing, fixation) እያለ ይሄዳል:: ድብድ ማለት የማይንቀሳቀስ፣ ባለበት የቆመ፣ የተቸከለ ማለት ነዉ::

ኢሲፒ (አንድ ላይ) ከሚለዉ የወላይትኛ ቃል ሲፓ (same) የሚለዉን ቃል እናገኛለን:: ሲፓ ማለት ያዉ ወይም «አንድ ዓይነት» ማለት ነዉ::

«ዉነት ነዉ ብሎ ወሰደ» ከሚለዉ ሐረግ ወነመነ (assume) የሚለዉን ግስ እናገኛለን:: ግሱም ሲረባ ወነመነ፣ ዉንምን (assumed)፣ ወንማኝ፣ ዉንመና (assumption, assuming) እያለ ይሄዳል:: ወነመነ ማለት ገመተ፣ ይሆናል ብሎ ተቀበለ እንደ ማለት ነዉ:: «ወነመነ» እና «ወመነ» ሊምታቱብህ አይገባም፣ ለመወመን (ወመኔ ለመሆን) ካላሰብክ በስተቀር::

ፈካቲ (ምሳሌ) ከሚለዉ የኦሮምኛ ቃል ፎቸክ (model) የሚለዉን ቃል እናገኛለን:: ግሱም ሲረባ ፎቸከ (to model)፣ ፉችክ (modelled)፣ ፎቻኪ፣ ፉቸካ (modelling) እያለ ይሄዳል:: ፎቸከ ማለት ፎቸክ ሠራ ማለት ነዉ::

ሱራ (ሥዕል) እና ፈኪ (ሥዕል) የሚሉትን የኦሮምኛ ቃሎች በማጣመር ሱርፊክ (figure) የሚለዉን ቃል እናገኛለን:: ግሱም ሲረባ ሶረፈከ (to figure, figurate)፣ ሱርፍክ (figured)፣ ሶርፋኪ (figurater)፣ ሱርፈካ (figuration)፣ ሱርፊካዊ (figurative) እያለ ይሄዳል:: ሱርፊክ ማለት እንግዲህ ሥዕል (picture) እንደ ማለት ነዉ::

ቁስ እና ስበት የሚሉትን ቃሎች በማጣመር ቁስበት (gravity) የሚለዉን ቃል እናገኛለን:: ግሱም ሲረባ ቆሰበ፣ ቁስብ፣ ቆሳቢ፣ ቁሰባ (gravitation)፣ ቁስበታዊ (gravitational) እያለ ይሄዳል:: ቆሰበ ማለት ቁስበታዊ ኀይል (gravitational force) ገበረ፣ ወይም በቁስበታዊ ኀይል ሳበ እንደ ማለት ሲሆን የእንግሊዘኛ አቻ ግን የለዉም::

ኡባይካ (ሁሉም ነገር) ከሚለዉ የወላይትኛ ቃል ቫይካ (universe)፣ ቫይካዊ (universal) የሚሉትን ቃሎች ይሆናል:: ከዚህም ቫይካዊ ሕግ (universal law)፣ ቫይካዲን (university) የመሳሰሉትን ቃሎች እናገኛለን:: ለምሳሌ ያህል **የኒዉተን ቫይካዊ የቁስበት ሕግ** (Newton's law of universal gravitation) ይሆናል::

ተጨባጭነት ወይም ያለዉ ነገር ግዑዝ (physical) ይባላል:: የዚህ ተቃራኒ ደግሞ ምናባዊ (immaginary) ይባላል:: እነዚህን ቃሎች ከታጠቅን እንግዲህ ስለ ራማ ሉል (celestial sphere) እንደ ልባችን መጻፍ እንችላለን:: እነሆ::

## *ራማ ሉል*

ደመና አልባ በሆነ ምሽት ሰማይ ላይ ተቆጥረዉ የማይዘልቁ፣ ጉልቆ መሳፍርት የሌላቸዉ የሚመስሉ ኮኮቦች እንዳሸዋ ፈሰዉበት እንመለከታለን:: ቀያኒዉም (poet) ያለዉ

ኮኮቦችን የጠፈር፣ አሸዋን የወንዝ ዳር
እጽዋትን የዱር፣ ዛፍ ቅጠልና ሣር
ከፈጣሪ በስተቀር፣ ማን ነዉ የሚቆጥር?[23]

ነዉ:: እንደ ዉነቱ ከሆነ ግን የምናያቸዉ ኮኮቦች ቁጥር እጅግም ብዙ አይደለም:: አንድ ሰዉ ያለ ሩፓይፉ (telescope) ርዳታ በራቁት ዓይኑ (naked eye) ሊመለከታቸዉ የሚችለዉ ኮኮቦች ቁጥር በዛ ቢባል ካራት ሺ አይበልጥም::

እነዚህ ኮኮቦች ከምድር ያሏቸዉ ርቀቶች በሰፊዉ የተለያዩ ናቸዉ:: ለምሳሌ ያህል ከፀሐይ ቀጥሎ ለምድር ዠቅርብ (the nearest) የሆነዉ ኮኮብ ቅርብ ፈረሰብ (Proxima Centauri) ሲባል ይህም ኮኮብ ከምድር ያለዉ ርቀት 4.2 ብርሃን ዓመት (light year) ነዉ:: በሌላ አባባል ብርሃን ከቅርብ ፈረሰብ ተነስቶ ምድር ለመድረስ 4.2 ዓመታት ይፈጅበታል ማለት ነዉ:: በሌላ በኩል ግን ብርሃን ከፀሐይ ተነስቶ ምድር ለመድረስ የሚፈጅበት ጊዜ 8 ደቂቃ ብቻ ነዉ:: ስለዚህም ቅርብ ፈረሰብ ከምድር ያለዉ ርቀት ፀሐይ ከምድር ያላትን ርቀት 280 ሺ ጊዜ ገደማ ነዉ ማለት ነዉ:: ፈረሰብ የሚለዉ ቃል የተገኘዉ ፈረስ እና ሰብ (ሰዉ) የሚሉትን ቃሎች በማጣመር ነዉ::


ሌሎቹ ኮኮቦች ደግሞ ከምድር ያሏቸዉ ርቀቶች ባስሮች፣ በመቶወችና በሽወች የሚቆጠሩ የብርሃን ዓመታት ናቸዉ:: በተጨማሪ ደግሞ እነዚህ ኮኮቦች ባሉበት የቆሙ ሳይሆኑ ከምድርና ከርስበርሳቸዉ በሚያራርቋቸዉ ከፍተኛ ፍጥነቶች የሚጓዙ ግዙፍ አካሎች ናቸዉ::
ሆኖም ግን በራቁት ዓይን ስንመለከታቸዉ ሁሉም ኮኮቦች ከምድር ያሏቸዉ ርቀቶች አኩል፣ እንዲሁም በኮኮቦቹ መካከል ያሉት ርቀቶች ወልፌክ (constant) ማለትም ኢተለዋጭ መስለዉ ይታዩናል:: በሌላ አባባል ሁሉም ኮኮቦች ከምድር እኩል በሆነ ርቀት ላይ ባሉበት ሳይነቃነቁ ተተክለዉ ማለትም ድብድ (fixed) ሁነዉ የተቀመጡ ይመስለናል:: ይህ ማለት ደግሞ ኮኮቦቹ ከምድር አንጻርና ከርስበርሳቸዉ አንጻር የሚያካሂዷቸዉን ሑሰቶች በራቁት ዓይናችን ለመፈንገን (to detect) ማለትም ለማየት እንችልም ማለት ነዉ:: ለዚህም ምክኒያቱ ኮኮቦቹ ከምድር እጅግ በጣም ሩቅ መሆናቸዉ ነዉ:: ስለሆነም ኮኮቦቹ በሑሰታቸዉ ሳቢያ በተወሰነ የጊዜ እመርታ (time interval) እንበል ባንድ ዓመት ዉስጥ የሚጓዙት ርቀት፣ አሁን ከምድር ካላቸዉ ርቀት ጋር ሲነጻጸር እጅግ አናሳ ከመሆኑ የተነሳ ካሉበት እንዳልተጓዙ ማለትም እንዳልተንቀሳቀሱ አድርገን ልንቆጥራቸዉ እንችላለን::

የኮኮቦችን ድብድ (fixed) ማለትም ትክል ሁነዉ መታየት በሚከተለዉ ምሳሌ መረዳት እንችላለን:: በከፍተኛ ፍጥነት እንበል 1000 ሃቆ/ኑ (km/s) በሆነ ፍጥነት የሚጓዝን ኔፋልፒዳ (airplane) እንወሰድ:: ኔፋልፒዳዉ ባናታችን ላይ በሚያልፍበት ወቅት ፍጥነቱ ከፍተኛ እንደሆነ በቀላሉ እናስተዉላለን:: ኔፋልፒዳዉ ከኛ ርቆ ወደ አድማስ በሚቃረብበት ጊዜ ግን ጭራሹን የሚነቀሳቀስ አይመስለንም:: ለዚህም ምክኒያቱ ኔፋልፒዳዉ እንበል ባንድ ኑሲቃ (second) ዉስጥ የሚጓዘዉ ርቀት ከኛ ካለዉ ርቀት ጋር ሲነጻጸር ኢምንት መሆኑ ነዉ::
እንግዲህ ሰማይ ላይ የምንመለከታቸዉ የኮኮቦች ዱክፋኖች (patterns) ድብድ (fixed) ማለትም ትክል ሳይሆኑ ከጊዜ ጋር በማያቋርጥ ሁኔታ እየተለዋወጡ ያሉ ናቸዉ ማለት ነዉ:: ሆኖም ግን ኮኮቦቹ ከምድር እጅግ በጣም ሩቅ በመሆናቸዉ ሳቢያ የደክፋኖቻቸዉ ማለትም ያቀማመጣቸዉ ለዉጦች እጅግ በጣም ዝግተኛ ናቸዉ:: ከለዉጡም ዝግተኛነት የተነሳ በኮኮቦቹ ዱክፋኖች ላይ ጉልህ ለዉጥ የሚከሰተዉ በመቶ ሺ የሚቆጠሩ ዓመታት ካለፉ በኋላ ነዉ:: በሌላ አባባል ዛሬ እኛ ሰማይ ላይ የምናያቸዉ የኮኮቡች ዱክፋኖች ጥንታዊ ሰወች ከብዙ ሺ ዓመታት በፊት ይመለከቷቸዉ ከነበሩት ዱክፋኖች ጋር ከሞላ ጎደል ሲፓ (same) ማለትም ያዉ ናቸዉ ማለት ነዉ::

እንግዲህ ኮኮቦችን በራቁት ዓይን ከመመልከት አንፃር የሚከተሉትን ሁለት ዉንመናወች (assumptions) መዉሰድ እንችላልን ማለት ነዉ::

1. ሁሉም ኮኮቦች ከምድር ያሏቸዉ ርቀቶች እኩል ናቸዉ::
2. በኮኮቦች መካከል አንጻራዊ እንቅስቃሴ የለም:: ማለትም የኮከቦቹ ዱክፈኖች (patterns) ድብድ (fixed) ናቸዉ::

በሌላ አባባል ሁሉም ኮኮቦች ሱርሬክ (figure) 1 ላይ እንደተመለከተዉ ምድርን ማዕከሉ ባደረገና አክዘንን (radius) እጅግ በጣም ትልቅ በሆነ ግዙፍ ሉል (sphere) ላይ ያለመነቃነቅ ተቸክለዉ ይገኛሉ ብልን መወንመን (assume) እንችላለን ማለት ነዉ:: ይህም እጅግ በጣም ግዙፍ የሆነ ሉል፣ ራማ ሉል (celestial sphere) በመባል ይታወቃል::





ሱርሬክ 1: ራማ ሉል

እዚህ ላይ መገንዘብ ያለብን ዋናዉ ቁምነገር ራማ ሉል ኮኮቦች ሰማይ ላይ ያሏቸዉን ጠባዮች ለማጥናት የሚያገለግል ፎቸክ (model) እንጅ ግኡዝ (physical) አለመሆኑን ነዉ:: ማለትም ራማ ሉል በመባል የሚታወቅ፣ ኮከቦች በላዩ ላይ ሰፍረዉ የሚገኙበት ሉል በግኡዙ ቫይካ (physical universe) ዉስጥ የለም:: በሌላ አባባል ራማ ሉል ምናባዊ (immaginary) እንጅ ግዑዛዊ አይደለም::

የኮኮቦችን ጠባዮች ለማጥናት የሚያገለግሉ የተለያዩ ፎቸኮች አሉ:: ራማ ሉል ከነዚህ ፎቸኮች ዉስጥ ዠቀላሉ (the simplest) ማለትም እጅግ በጣም ቀላሉ ፎቸክ ነዉ::

## *ራማ አኳይ*

ራማ ሉል ምድርን ማዕከሉ ያደረገ እጅግ በጣም ግዙፍ ሉል ነዉ ብለናል:: አሁን እንግዲህ ምድርን እንደምትነፋ ፊኛ እንዉሰድና ልክ ራማ ሉልን እስከምተነካ ድረስ ተነፋች እንበል:: ይህ በሚሆንበት ጊዜ የምድር አኳይ (equator)፣ የራማ ሉል አኳይ (celestial equator) ይሆናል፣ የምድር ሰሜን ዋልታ የራማ ሉል ሰሜን ዋልታ (celestial north pole) ይሆናል፣ የምድር ደቡብ ዋልታ ደግሞ የራማ ሉል ደቡብ ዋልታ (celestial south pole) ይሆናል:: ይህ ሁኔታ ሱርሬክ 2 ላይ ተመልክቷል::




ሱርሬክ 2: ራማ አኳይ

በሌላ አባባል፣ የምድር አኪይ ማለት በምሥራቅ-ምዕራብ አቅጣጫ ምድርን ለሁለት እኩል ግማሾች የሚከፍል ምናባዊ መስመር (immaginary line) እንደሆነ ሁሉ፣ ራማ አኪይ ማለት ደግሞ የምድርን አኪይ ተከትሎ በምስራቅ-ምዕራብ አቅጣጫ ራማ ሉልን ለሁለት እኩል ግማሾች የሚከፍል ምናባዊ መስመር ነዉ ማለት ነዉ:: እንዲሁም ራማዊ ሰሜን ዋልታ በትክክል ከምድር ሰሜን ዋልታ አናት ላይ የሆነ የራማ ሉል ነቁጥ ሲሆን፣ ራማዊ ደቡብ ዋልታ ደግሞ በትክክል ከምድር ዋልታ አናት ላይ የሆነ የራማ ሉል ነቁጥ ነዉ ማለት ነዉ::

የምድር አኪይ ምድርን ለሁለት እኩል ንፍቀሉሎች (hemispheres)፣ ማለትም ሰሜን ንፍቀሉል (northern hemisphere) እና ደቡብ ንፍቀሉል (southern hemisphere) እንደሚከፍላት ሁሉ፣ ራማ አኪይም ራማ ሉልን ለሁለት እኩል ንፍቀሉሎች ይከፍለዋል:: ከራማ አኪይ በስተሰሜን የሚገኘዉ ንፍቀሉል ራማዊ ሰሜን ንፍቀሉል (celestial northern hemisphere) ወይም ሰሜናዊ ሰማይ (northern sky) ሲባል፣ ከራማ አኪይ በስተደቡብ የሚገኘዉ ንፍቀሉል ደግሞ ራማዊ ደቡብ ንፍቀሉል (celestial southern hemisphere) ወይም ደቡባዊ ሰማይ (southern sky) ይባላል:: ራማዊ ሰሜን ዋልታ በሰሜናዊ ሰማይ ላይ ሲገኝ፣ ራማዊ ደቡብ ዋልታ ደግሞ በደቡባዊ ሰማይ ላይ ይገኛል::

በምድር ሰሜናዊ ንፍቀሉል ዉስጥ የሚገኙትን መላዉን እስያ፣ መላዉን አወሮጳ፣ መግሪጳን (Green land)፣ ሰሜን አሜሪቃንና፣ አገራችንን ቅድስት ጦቢያን ጨምሮ በላጨን ያፍሪቃ ክፍል የሚሸፍነዉ ሰማይ ሰሜናዊ ሰማይ ሲሆን፣ በምድር ደቡባዊ ንፍቀሉል ዉስጥ የሚገኙትን ደቡብ አሜሪቃን፣ አዉስትራሊያን፣ ያፍሪቃን ሲሶ (በቅርቦዛ) እና የተለያዩ ደሴቶችን የሚሸፍነዉ ሰማይ ደግሞ ደቡባዊ ሰማይ ነዉ:: መግሪጳ (Green land) የሚለዉ ቃል የተገኘዉ መገርሳ (አርንጓዴ) ከሚለዉ የኦሮምኛ ቃል ነዉ:: መግሪጳ ማለት በአፍሪኖስ (Atlantic ocean) እና ሰዋልኖስ (Arctic ocean) መካከል የሚገኝ በዴንማርኮች የሚተዳደር ምድር ነዉ::

«አትላንቲክ ዉቅያኖስ» (Atlantic Ocean) በመባል የሚታወቀዉ ዉቅያኖስ በመሠረቱ ባፍሪቃ ተሰይሞ «አፍሪቃ ዉቅያኖስ» መባል ነበረበት:: እኔም ካሁን በኋላ ማንም ተከተለኝም አልተከተለኝም፣ ማንም ሰማኝም አልሰማኝም፣ ማንም ተረዳኝም አልተረዳኝም የምጠራዉ በዚህ ስሙ ነዉ:: ይህ ዉቅያኖስ በናት አፍሪቃ ያልተሰየመበት ምክኒያት ሌላ ምንም ሳይሆን ትናንት መጤዉ ነጭ ላፍሪቃ ካለዉ መሠረተ ቢስ ከፍተኛ ንቀት የተነሳ ብቻና ብቻ ነዉ:: «አፍሪቃ ዉቅያኖስ» ባጭሩ አፍሪኖስ ሊባል ይችላል:: አፍሪቃ እና ደሴት የሚሉትን ቃሎ በማጣመር አፍሪሴት (Atlantis) የሚለዉን ቃል እናገኛለን:: አፍሬሴት ማለት ባፈታሪክ መሠረት አፍሪቃንና አዉሮጳን አጠቃላ ትገዛ የነበረችና ዉቅያኖስ ዉስጥ ሰምጣ የጠፋች ደሴት ናት::

ሰሜን ዋልታ እና ጌ (ምድር) የሚሉትን ቃሎች በማጣመር ሰዋልጌ (Arctic) የሚለዉን ቃል እናገኛለን:: ከዚህም ሰዋልጌ ዉቅያኖስ ወይም ባጭሩ ሰዋልኖስ (Arctic Ocean)፣ ሰዋልጌ ክብ (Arctic circle)፣ ሰዋልጌ ክልል (Arctic rgion) የሚሉትን ቃሎች እናገኛለን:: ደቡብ ዋልታ እና ጌ (ምድር) የሚሉትን ቃሎች በማጣመር ደዋልጌ (Antartic) የሚለዉን ቃል እናገኛለን:: ከዚህም ደዋልጌ ዉቅያኖስ ወይም ባጭሩ ደዋልኖስ (Antartic Ocean)፣ ደዋልጌ ክብ (Antartic circle)፣ ደዋልጌ ክልል (Antartic rgion)፣ ደዋልጊያ (Antartica)፣ ደዋልጌ የብሲላስ (Antartic peninsula) የሚሉትን ቃሎች እናገኛለን:: የብሲላስ (peninsula) የሚለዉ ቃል የተገኘዉ የብስ (ደረቅ መሬት) እና ምላስ የሚሉትን ቃሎች በማጣመር ነዉ:: ስለዚህም የብሲላሳዊ (peninsular) ይሆናል::


እግረመንገዳችንን ኩሽ ከሚለዉ ቃል ኩሽ ዉቅያኖስ ወይም ባጭሩ ኩሽኖሽ (Indian Ocean) የሚለዉን ቃል እናገኛለን:: እንዲሁም ሰላማዊ ዉቅያኖስ ወይም ባጭሩ ሰላምኖስ (Pacific Ocean) ይሆናል:: በተጨማሪም «ዐብይ ባሕር» የሚለዉን ሐረግ በማሳጠር ዐቢባር (Mediterranean sea) የሚለዉን ቃል እናገኛለን:: በግእዝም ይህ ባሕር የሚታወቀዉ «ዐብይ ባሕር» (ትልቁ ባሕር) በመባል ነዉ (ትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ 7 ቁጥር 2 ይመልከቱ):: ዉቅያኖሶች እና ዐቢባር በድጋሚ በሚከተለዉ ሰንጠረዥ ላይ ተዘርዝረዋል::

| ዉቅያኖሶችና ዐቢባር | | | |
|---|---|---|---|
| antarctic ocean | ደዋልኖስ | indian ocean | ኩሽኖስ |
| arctic ocean | ሰዋልኖስ | mediterranean sea | ዐቢባር |
| atlantic ocean | አፍሪኖስ | pacific ocean | ሰላምኖስ |

## *ኩልኩት እና ሩንጋ*

ኮለኮለ (ደረደረ) ከሚለዉ ያማረኛ ቃል ኩልኩት (parallel) የሚለዉን ቃል እናገኛለን:: ግሱም ሲረባ ኮለኮተ (make or become parallel)፣ ኩልኩት፣ ኮልኳች፣ ኩልኮታ እያለ ይሄዳል:: ለምሳሌ ያህል ኩልኩት መስመሮች (parallel lines) ማለት ምንም ያህል ቢረዝሙ የማይገናኙ መስመሮች፣ ማለትም በመካከላቸዉ ያለዉ ርቀት የትም ቦታ ላይ ሲፓ (same) የሆነ መስመሮች ማለት ነዉ:: ኩልኩል ከሚለዉ ቃል ይልቅ ኩልኩት የሚለዉን ቃል የመረጥኩበት ምክኒያት ሲረባ ኮለኮለ (እንዲስቅ አደረገ) ከሚለዉ ቃል ጋር እንዳይምታታ ነዉ::

ሮጋ (ማእዘን) ከሚለዉ የኦሮምኛ ቃል ሩንጋ (perpendicular) የሚለዉን ቃል እናገኛለን:: ግሱም ሲረባ ረነገ (make or become perpendicular)፣ ርንግ፣ ረናጊ፣ ርነጋ እያለ ይሄዳል:: ለምሰሌ ያህል ሩንጋ መስመሮች (perpendicular lines) ማለት ሲገናኙ $90^\circ$ ዘዌ (angle) የሚሠሩ መስመሮች ማለት ነዉ:: ኩልኩትና ሩንጋ መስመሮች ሱርፌክ 3 ላይ ተመልከተዋል::





ሱርፌክ 3: ኩልኩትና ሩንጋ መስመሮች

## *አድማስ እና ቁንጮማስ*


አድማስ (horizon) ሰማይና ምድር የሚገናኙበትን የሚወክል ግዙፍ አግዳሚ ክብ (circle) ነዉ:: በሌላ አባባል አድማስ ማለት ሰማይና ምድርን የሚያካልል ድንበር ማለት ነዉ::

ቁንጮማስ (zenith) ማለት ባናት ትክክል የሚገኝ የሰማይ ነቁጥ (point) ነዉ:: በሌላ አባባል ቁንጮማስ ከአድማስ $90^\circ$ የሚሠራ የሰማይ ነቁጥ ነዉ፣ ማለትም ባድማስና በቁንጮማስ መካከል ያለዉ ዘዌ (angle) ሁልጊዜ $90^\circ$ ነዉ:: ቁንጮማስ የሚለዉ ቃል የተገኘዉ «ቁንጮ» እና «አድማስ» ከሚሉት ቃሎች ነዉ:: አድማስና ቁንጮማስ ሱርፌክ 4 ላይ ተመልክተዋል::





ሱርፌክ 4: አድማስና ቁንጮማስ

ያንድ ነጻሪ (observer) ማለትም ተመልካች አድማስ ነጻሪዉ ከቆመበት ቦታ ላይ ይመካል:: ለምሳሌ ያህል ሱርፊክ 5 ላይ እንደተመለከተዉ አንድ ነጻሪ ከምድር ሰሜን ዋልታ ላይ ቢቆም የነጻሪዉ አድማስ ለምድር አኳይ (እንዲሁም ለራማ አኳይ) ኩልኩት (parallel) ሲሆን፣ ቁንጮማሱ ደግሞ ለምድር አኳይ (እንዲሁም ለራማ አኳይ) ሩንጋ (perpendicular) ይሆናል:: ምድር ሰሜን ዋልታ ላይ ለቆመ ነጻሪ ቁንጮማሱ የራማ ሉል ሰሜን ዋልታ ሲሆን፣ ምድር ደቡብ ዋልታ ላይ ለቆመ ነጻሪ ደግሞ ቁንጮማሱ የራማ ሉል ደቡብ ዋልታ ነዉ::





ሱርፊክ 5: ሰሜን ዋልታ ላይ የቆመ ነጻሪ አድማስና ቁንጮማስ::

በተመሳሳይ ሁኔታ ሱርፊክ 6 ላይ እንደተመለከተዉ አንድ ነጻሪ ምድር አኳይ ላይ ቢቆም የነጻሪዉ አድማስ ለምድር አኳይ (እንዲሁም ለራማ አኳይ) ሩንጋ (perpendicular) ሲሆን፣ ቁንጮማሱ ደግሞ ለምድር አኳይ (እንዲሁም ለራማ አኳይ) ኩልኩት (parallel) ይሆናል::




ሱርፊክ 6: ምድር አኳይ ላይ የቆመ ነጻሪ አድማስና ቁንጮማስ::

አንድ ነጻሪ በምድር አኳይና በሰሜን ዋልታ (ወይም ደቡብ ዋልታ) መካከል ቢቆም ደግሞ የነጻሪዉ አድማስና ቁንጮማስ ሁለቱም ከራማ አኳይ ጋር በ 0° እና 90° መካከል የሆኑ ዘዌወችን (angles) ይሠራሉ።  ይህ ሁኔታ ሱርፊክ 7 ላይ ተመልክቷል።





ሱርፊክ 7: በምድር አካይና በሰሜን ዋልታ መካከል የቆመ ነጻሪ አድማስና ቁንጮማስ።

## ዝቅዝቀትና ቀኝ ዕርገት

ምድር ገጽ ላይ የሚገኝ የማናቸዉም ቦታ ቅምጠት (position) የቦታዉን ጋድምገር (latitude) እና ቋሚገር (longitude) በመስጠት ይገለፃል።  ጋድምገር የሚለዉ ቃል የተገኘዉ «አግዳሚ ማገር» ከሚለዉ ሐረግ ሲሆን፣ ቋሚገር የሚለዉ ቃል የተገኘዉ ደግሞ «ቋሚ ማገር» ከሚለዉ ሐረግ ነዉ። ለምሳሌ ያህል የቅድስቲቷ ከተማ የላሊበላ ቅምጠት ጋድምገሩ 12°12' ሰ ሲሆን ቋሚገሩ ደግሞ 39°12' ም ነዉ።  መዲናችን አዲሳባ ደግሞ በጋድምገር 9°2'ሰ እና በቋሚገር 38°42' ም ላይ ትገኝለች።  እዚህ ላይ ፊደል «ሰ» እና «ም»፣ እንደቅደምተከተላቸዉ፣ «ሰሜን» እና «ምሥራቅ» የሚሉትን ቃሎች ይወክላሉ።

በተመሳሳይ ሁኔታ ራማ ሉል ላይ የሚገኝ የማናቸዉም ራማዊ አካል (celestial body) ቅምጠት ያካሉን ዝቅዝቀት (declination) እና ቀኝ ዕርገት (right ascension) በመስጠት ይገለጻል።  ስለ ዝቅዝቀትና ቀኝ ዕርገት ወደፊት በሌላ ጦማር ላይ በሰፊዉ እንወያያለን።  ባጭሩ ለመናገር ግን ዝቅዝቀት የጋድምገር ራማዊ አቻ ሲሆን፣ ቀኝ ዕርገት ደግሞ የቋሚገር ራማዊ አቻ ነዉ።  በሌላ አባባል ዝቅዝቀት በራማ ሉል ላይ የሚጫወተዉ ሚና ጋድምገር በምድር ገጽ ላይ የሚጫወትዉን ሚና አቻ ነዉ ሲሆን፣ ቀኝ ዕርገት በራማ ሉል ላይ የሚጫወተዉ ሚና ደግሞ ቋሚገር በምድር ገጽ ላይ የሚጫወትዉን ሚና አቻ ነዉ።  ይህም ሁኔታ ሱርፊክ 8 ላይ ተመልክቷል።




ሱርፊክ 8: የራማዊ አካሎች ቅምጠት አገላለጽ።

ስላነበቡኝ **አኮቴ** (thanks)::   በሌላ ጦማር (article) እስከምንገናኝ ድረስ ደህና ይሰንብቱ:: አብሔር (God) - የጦቢያ አምላክ - ይጠብቅወ::  አኮተ ማለት በግእዝ አመሰገነ፣ ከፍ ከፍ አደረገ ማለት ነዉ፣ «**ነአኩተከ እግዚኦ**» (አቤቱ እናመሰግንሃለን) እንዲል «**ጸሎት ዘዘወትር**» (የዘወትር ጸሎት)::  ግሱም ሰረባ አኮተ (to thank)፣ አኩተ (thanked) ፣ አኳች (one who thanks)፣ እኮታ (thanking) እያለ  ይሄዳል::  እንግዲህ አኮቴ የሚለዉ ቃል - አመሰግናለሁ ከሚለዉ የተንዛዛ ቃል ይልቅ ቅልብጭ ያለ ስለሆነ - እኮታ እንዲለምድብን - ለተደረገልን ነገር ሁሉ እንድናኩት - የራሱን እገዛ ያደርጋል ማለት ነዉ::  በሌላ አባባል ክታዊ (formal)[24] ዉዳሴን ለመግለጽ «አመሰግናለሁ»ን ፣ ወትራዊ (informal) ዉዳሴን ለመግለጽ ደግሞ እጥር፣ ምጥን ያለዉን «**አኮቴ**»ን መጠቀም እንችላለን ማለት ነዉ::

*መስፍን አረጋ ዘብሔረ ኩሽ*
*የትብቱ ቀብር ደሴ - ሳላይሽ::*

mesfin.arega@gmail.com

---

[1] *መዕሐፈ ሄኖክ ምዕራፍ 22 ቁጥር 5::*
[2] *ዝኒከም፡ ምዕራፍ 21 ቁጥር 57::* ዝኒከም (ibid) ማለት አንደቀድሞዉ፣ እዚያዉ ቦታ ማለት ሲሆን የተገኘዉም ዝኒ ከማሁ (እዚያዉ ቦታ፣ አንደዚያዉ) የሚለዉን የግዕዝ ቃል በማሳጠር ነዉ::
[3] *ዝኒከም፡ ምዕራፍ 23 ቁጥር 14::*
[4] *ዝኒከም : ምዕራፍ 26::*
[5] *ዝኒከም፡ ምዕራፍ 24 ቁጥር 8::*
[6] ዝኒከም፡ *ምዕራፍ 23 ቁጥር 20::*
[7] ዝንከም፡ *ምዕራፍ 21 ቁጥር 18 እስከ 22::*
[8] *መጽሐፈ መክብብ ምዕራፍ 1 ቁጥር 10::*
[9] «ምድር ሁሉ ባንድ ቋንቋና ባንድ ንግግር ነበረች»፣ ኦሪት ዘፍጥረት፣ ምዕራፍ 11 ቁጥር 1::
[10] "The Europeans gave us bibles only so that, when we close our eyes to pray, they can take our land" (Jommo Kenyata)
[11] "The Wuhabists give us the Koran only so that, when we kneel down to pray, they can chop our heads off and completely arabize Africa" (Mesfin Arega)
[12] **አንጋፋ** የኦሮምኛ ቃል ሲሆን ትርጉሙም የመጀመርያ ልጅ (በኩር) ማለት ነዉ::  ባማረኛ ግን አንጋፋ ማለት ዋና፣ አብይ፣ ትልቅ እንደ ማለት ነዉ::
[13] ፅንሰ-ሐሳብ የሚለዉን ቃል ለማርባት ይመች ዘንድ በማሳጠር **ፅንሳብ** (concept,conception) የሚለዉን ቃል እናገኛለን:: ግሱም ሲረባ ፀነሰበ (conceptualizስ)፣ ፅንስብ (conceptualized)፣ ፀንሳቢ (conceptualizer)፣ ፅንሰባ (conceptualization)፣ ፅንሳባዊ (conceptual)  እያለ ይሄዳል::  ፅንሰባ ማለት ባይምሮ ዉስጥ ፅንሳብ መመሥረት - መፀነስ - ማለት ነዉ::
[14] **ዐላዊ** (ግእዝ) = ወንጀለኛ፣ እምቢተኛ፣ ሽፍታ፣ ለዋጭ፣ ገልባጭ::
[15] **ሐሳዊ** (ግእዝ) = ዋሾ፣ ቀጣፊ፣ ሐሰተኛ፣ ከሓዲ::
[16] **ምፀት** = ተረብ፣ ግልባጭ ወሬ፣ በሬ ወለደ::  «ያባ ደባ ደቦ ስልቻ ጤፍ ይቋጥራል፣ ባቁላ ያፈሳል» እንዲሉ::
[17] **ለበጠ** = ሐሰትን እዉነት አስመሰለ፣ ሸረደደ::  **ለበጣ** ማለት ደግሞ ሸንገላ፣ ሽርደዳ፣ ምፀት ማለት ነዉ::
[18] **አሕዛብ** = በፍጡር የሚያመልኩ፣ ለጣዖት የሚሰግዱ፣ ጨካኝና አረመኔ የሆኑ ቁጥራቸዉ የበዛ ሕዝቦች::  አሕዛቦች ያማረኛ ሲሆን፣ አሕዛብ  የግእዝ ነዉ::
[19] **ፏደደ** =  ሮጠ፣ ፈጠነ፣ ሸመጠጠ::  ስለዚህም **ፏዳጅ** ማለት ሯጭ ማለት ይሆናል::
[20] **ቀየደ** = አንገትንና የኋላ እግርን፣ ወይም የፊት እግርንና የኋላ እግርን በማቆራኘት አሰረ፣ ሰነከለ::  «እንዳትበላ ለጎሚት፣ እንዳትሄድ ቀየዷት» እንዲሉ::
[21] **ፍንጅ** (handcuff)  = ሁለት እጅ አጣምሮ ለማሰርያ የሚሆን ጥንድ የሰንሰለት ቀለበት::  «እሰር በፍንጅ፣ ጣል በደጅ» እንዲሉ::
[22] **ለፈፈ** = ለፈለፈ፣ እየዞረ በጩኸት ተናገረ፣ ዐዋጅ አሰማ:: «**ልፋፈ ጽድቅ**» ማለት ደግሞ ተጽፎና ተጠቅልሎ በሰዉ ዐንገት ላይ የሚንጠለጠል መንፈሳዊ ክታብ ማለት ነዉ::
[23] ደርዛቪን (Derzhavin) የሚባለዉ ራሽያዊ ባለቅኔ አብሔር (God) በሚል ርዕስ ከገጠመዉ ግጥም የተወሰደ::

" Count grains of sand, and planet's rays
Eventhough a lofty mind were able"

[24] ክተኛ፣ ክታዊ (formal, formalistic) ማለት ስነስርዓታዊ፣ ደንብን የጠበቀ እንደማለት ሲሆን ቃሉ የተገኘዉም የክት (ተከቶ የሚቀመጥ፣ በባዕል ብቻ የሚለበስ) ከሚለዉ ያማረኛ ቃል ነዉ። ከዚህም ክተኛነት፣ ክትፍና (formalism)፣ ክተኛ፣ ክትፈናኝ (formalist)፣ ክታዊነት፣ ክትነት (formality)፣ ክተኛ ሲንሲን (formal logic) የሚሉትን ቃሎች እናገኛለን። ግሱም ሲረባ ከተነ (formalize)፣ ክትን (formalized)፣ ከታኝ (formalizer)፣ ክተና (formalization) እያለ ይሄዳል።

በተመሳሳይ ሁኔታ ወትረኛ፣ ወትራዊ (informal) ማለት ደንብን ያልተከተለ ማለት ሲሆን ቃሉ የተገኘዉም ወትሮ (ዘወትር፣ በየጊዜዉ) ከሚለዉ ያማረኛ ቃል ነዉ። ከዚህም ወትራዊነት፣ ዉትረት (informality) የሚለዉን ቃል እናገኛለን። ግሱም ሲረባ ወተረገ (make informal)፣ ዉትርግ፣ ወትራጊ፣ ዉትረጋ እያለ ሲሄድ የእንግሊዘኛ አቻ ግን የለዉም።